የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 9
Addis Ababa March 16/ 2023

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፱/፪ሺ፲፭**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች አሠራርና አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ ደንብ**

ገፅ……………………………………፫፻፸፫

**CONTENT**

**Regulation No.9/2023**

**A regulation to provide for Addis Ababa city Administration the functioning and organization of Ethics liaison units**

Page………………………………………373

## ደንብ ቁጥር ፱/፪ሺ፲፭

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች አሠራርና አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ተቋማት ውስጥ እየተንሰራፋ የመጣውን የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመታገል የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በየተቋማቱ የተቋቋሙ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሰራር፣ አደረጃጀት እና ከኮሚሽኑ ጋር የሚኖራቸውን የግንኙነት ሥርዓት መወሰን በማስፈለጉ፤

## Regulation No.9/2023

## A regulation to provide for Addis Ababa city Administration the functioning and organization of Ethics liaison units

**WHEREAS**, it's found necessary to fight corruption and mal-practices which is wide spreading in Addis Ababa city administration by determining practices and organization of ethics liaison units established in every institutions and their relationship with the Commission there by ascertaining benefit of the people;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፬ ንዐስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሀ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች አደረጃጀት እና አሰራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፰/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ምክር ቤት"** ማለት የከተማው ምክር ቤት ነው፤

፬. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፭/፪ሺ፲፬ ነው፤

፭. **"ኮሚሽን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፤

**NOW, THEREFORE**, in accordance with sub Article (1) and letter (a) of Article 14 of The Addis Ababa city administration revised charter proclamation number 361/2003 (as amended) , and of sub Article (1) of Article 22 of The Addis Ababa City Government Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation No 75/2022 ,the city council has issued this regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "A regulation to provide for Addis Ababa city Administration the functioning and organization of Ethics liaison units No.8/2023"

2. **Definition**

Unless the context requires otherwise in this regulation:

1. **"City"** means the Addis Ababa city;
2. **"Administration"** means the Addis Ababa City administration;
3. **"Council"** means the Council of the city;
4. **"Proclamation"** means the Addis Ababa City Government Ethics and Anti-Corruption Commission Establishment Proclamation Number 75/2022.
5. **"Commission"** means the Addis Ababa City Government Ethics and Anti-Corruption Commission;

፮. **"ኮሚሽነር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽንን ኃላፊነት የሚመራ ሰው ነው፤

፯. **"ምክትል ኮሚሽነር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽንን በምክትል ኃላፊነት የሚመራ ሰው ነው፤

፰. **"የመንግሥት መሥሪያ ቤት"** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በአስተዳደሩ በጀት የሚተዳደርና የከተማ አስተዳደሩ ሥራዎች የሚከናወኑበት ማናቸውም መስሪያ ቤት ነው፤

፱. **"የመንግሥት የልማት ድርጅት"** ማለት የአስተዳደሩ የባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የአስተዳደሩ የልማት ድርጅት ወይም የአክሲዮን ማኅበር ነው፤

፲. **"ተቋም"** ማለት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ የሚሰራበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ነው፤

፲፩. **"የተቋሙ የበላይ ኃላፊ"** ማለት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ የሚሰሩበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅትን የሚመራ የስራ ኃላፊ ነው፣

፲፪. **"የመንግስት ሠራተኛ"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት በቋሚነት ወይም በጊዚያዊነት ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ የሚሠራ ሰው ነው፤

6. **"Commissioner"** means a person who leads the Addis Ababa City administration Ethics and Anti-Corruption Commission;

7. **"Deputy Commissioner"** means a person who leads the Addis Ababa City administration Ethics and Anti-Corruption Commission as a deputy;

8. **"Public Office"** means any office that fully or partially run its activities by the budget of the city administration where by the activities of the city administration are carried out;

9. **"Public Enterprise"** means a public enterprise or share company where the city administration has a full or partial ownership;

10. **"Institution"** means a public office or public enterprise in which ethics liaison unit works on;

11. **"head of the institution"** means the head of the a public office or public enterprise in which ethics liaison unit works in;

12. **"Civil servant"** means a person who is employed permanently or temporarily in accordance with the civil servants proclamation of the city administration;

፲፫."**የልማት ድርጅት ሠራተኛ**" ማለት በአስተዳደሩ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም በውስጥ በቋሚነት በጊዜያዊነት የሚሠራ ሰው ነው፤

፲፬."**ዓላማ ፈፃሚ**" ማለት የሥነ-ነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተደራጁባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም ውስጥ የተቋሙን ዓላማ ለማሳካት የተዳራጁትን ዋና ዓላማ ፈፃሚ የስራ ሂደት ነው፣

፲፭."**በዓላማ ፈጻሚ ትይዩ የስራ ደረጃ**" ማለት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚኖራቸው የሥራ ደረጃ በተደራጁባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የተቋሙን ዓላማ ለማሳካት በተደራጁት ዓላማ ፈፃሚ የስራ ክፍሎች በከፍተኛው የተሰጣቸውን የስራ ደረጃ በእኩል ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ማለት ሲሆን ፡-

ሀ) በማዕከል ተቋማት በተቋሙ ካሉ አላማ ፈፃሚዎች ትልቁ ደረጃ ከያዘው ትይዩ ፤

ለ) በክፍለ ከተማ ሲሆን በክፍለ ከተማው ካሉ ጽህፈት ቤቶች ውስጥ ትልቁን የስራ ደረጃ ትይዩ፤

ሐ) በወረዳ ሲሆን በወረዳው ካሉ ጽህፈት ቤቶች ውስጥ ትልቁን የስራ ደረጃ ትይዩ ይሆናል ማለት ነው፡፡

13. **"employee of public enterprise"** means a person who is a permanent or temporary employee in public enterprises of the city administration;

14. **"Objective executor"** means a work stream inside public office or public enterprise in which ethics liaison unit is organized which is organized to attain the main objectives of the institution;

15. **"work level parallel to objective executor"** means the job level of ethics monitoring units in the public offices or public enterprise where they are organized the job level at the same or similar level as the highest assigned work units in order to achieve the purpose of the institution:

a) In the central institutions, parallel to the of institution's highest level objective executor;

b) In a sub-city, parallel to the highest level of work among the offices in the sub-city; and

c) If it is in a district, it shall be parallel to the highest work level of the offices in the district.

፲፮."**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. **የፆታ አገላለፅ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

፬. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት መሥሪያ ቤት እና የልማት ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች

፭. **ስለመደራጀት**

፩. በተቋማት ውስጥ የሥነ-ምግባር ጉዳዮችን የሚያስተባብሩና የየተቋማቱን የበላይ ኃላፊዎች የሚያማክሩ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች በአዋጁ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በዚህ ደንብ ተደራጅቷል፤

፪. ኮሚሽኑ በተቋማት ውስጥ ያለውን የሥራ ስፋት፣ የሚንቀሳቀሰውን የሃብት መጠን፣ የሰው ኃይል እና በሥራው ባህርይ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያለውን ተጋላጭነትን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚያስፈልገውን አደረጃጀት እና የሰው ሀይል ብዛት ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር ይወስናል፤

፫. በተቋማት ውስጥ የሚደራጀው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክቶሬት ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ በተደራጀበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ውስጥ በአለው የዓላማ ፈፃሚ ከፍተኛው የዳይሬክቶሬት ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ ደረጃ ይሆናል፤

16. "**Person**" means any natural or juridical person.

3. **Gender Expression**

In this regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

4. **Scope of application**

This regulation shall be applicable on public office and public enterprise of the city.

## PART TWO

## Ethics liaison units

5. **Organization**

1. Ethics liaison units that coordinate ethical matters in institutions and advise the heads of each institution are organized in this regulation according to sub article (1) of Article 19 of the proclamation;
2. The Commission shall in consultation with the relevant body, taking into account the scope of work in the institutions, the amount of resources, manpower and the vulnerability of the nature of the work to corruption and malpractice ,determine the necessary organization and the number of human resources ;
3. The directorate or team or professional of the ethics liaison unit organized in institutions shall be equivalent with the level of highest objective executor level of the directorate or group or professional in the public office or public enterprise;

፬. በቅርንጫፍ ደረጃ የሚደራጀው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክትሬት ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ በተደራጀበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም ቅርንጫፍ ውስጥ እንደየ አግባብነቱ በአለው የዓላማ ፈፃሚ ከፍተኛው የዳይሬክቶሬት ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ ደረጃ ይሆናል፤

፭. በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት ልማት ድርጅት ውስጥ የሚደራጀው የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ዳይሬክቶሬት፣ ቡድን እና የባለሙያ ስያሜ ኮሚሽኑ በሚሰይመው ስያሜ መሰረት ይሆናል፡፡

## ፮. <u>ዓላማዎች</u>

የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሯቸዋል፡-

፩. ሠራተኛውን በፀረ ሙስና ትምህርቶች፣ በሥራ ዲሲፕሊን በሙያ ሥነ-ምግባር ፣ በህዝብ አገልጋይነትና በኃላፊነት ስሜት በማነጽ የነቃና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ሠራተኛና ኃላፊ እንዲፈጠር ማድረግ፤

፪. በየተቋማቱ የሙስና ወንጀልንና ብልሹ አሰራርን የመከላከል፤

፫. በየተቋሙ የሚገኙ የመንግሥት ተሿሚዎች፣ የበላይ ኃላፊዎች ፣ ሠራተኞች እና የመንግሥት ልማት ድርጅት የበላይ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ እና የተመዘገበውን በየጊዜው እንዲያድሱ የማድረግ፤

4. The level of directorate or team or professional of the ethics liaison unit organized as a branch shall be equivalent with the level of the highest directorate or group or professional level according to the relevant objective executor in the public office or public enterprise or branch where it is organized;

5. The directorate, team and professional designation of the ethics liaison unit organized in a public office or public enterprise shall be based on the designation given by the commission.

## 6. <u>Objectives</u>

Ethics liaison units shall have the following objectives:

1. endeavour to create public employee and manager who do not condone corruption by promoting ethics and anti-corruption education work discipline professional ethics consciousness of serving the public and sense of duty among employees;
2. Prevent of corruption and malpractice in each institution;
3. To make government appointees, superiors, employees and superior officials and employees of the public enterprise in each institution to notify and register their property and renew their registered property regularly;

፬. የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ፣ እንዲመረመርና በአጥፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ጥረት የማድረግ፡፡

፯. **አቋም**

፩. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል በኃላፊ ወይም በሥነ-ምግባር መከታተያ ሠራተኛ የሚመራ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ሠራተኞች ሊኖሩት ይችላል፤

፪. መሥሪያ ቤቱ ወይም ድርጅቱ ቅርንጫፎች ካሉት እንደአስፈላጊነቱ የቅርንጫፍ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ይቋቋማሉ፡፡

፰. **ተጠሪነት**

፩. በአዋጁ አንቀጽ ፲፱. ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነት ለኮሚሽኑ ይሆናል፤

፪. የቅርንጫፍ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ተጠሪነት ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ ወይም ለዋናው ተቋም የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ይሆናል፡፡

፱. **ተግባራት**

የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል፡-

፩. የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎች፣ የፀረ-ሙስና ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች፣ የመልካም ሥነ ምግባር የሙስና አስከፊ ገጽታዎችና ጎጂነት ግንዛቤ እንዲያዳብር ያደርጋል፤

4. endeavour to cause acts of corruption and impropriety by exposed and investigated and appropriate actions are taken against the perpetrators .

7. **Organization**

1. The ethics liaison unit shall be headed by the head of ethics liaison unit or an ethics liaison unit employee and may have other employees as it deems necessary;
2. where the public office or public enterprise has branch office, branch ethics liaison units shall be established as may be necessary.

8. **Accountability**

1. According to sub article (2) of article 19 of the proclamation, the accountability of the ethics liaison unit will be to the commission;
2. The accountability of the branch ethics liaison unit shall be to the head of the ethics liaison unit of the public office or public enterprise or the main institution.

9. **Functions**

An ethics liaison unit shall have the following functions;

1. raise the awareness of officials and employees of the public office or the public enterprise on anti-corruption law, regulation and directives, good conduct and the harmful effects of corruption;

፪. የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎች ፣ የፀረ-ሙስና ሕጎች፣ የመስሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን ይከታተላል፤ ስለአፈፃፀማቸውም የመሥሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የበላይ ኃላፊ ያማክራል፤

፫. ኮሚሽኑ የሚያወጣውን የሥነ-ምግባር ደንብ መርህን ተከትሎ የመሥሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያ አግባብነት ካላቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ በተቋሙ ያፀድቃል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፬. መሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የሙስናና የብልሹ አሰራር ቀዳዳ የሚከፍቱ አሰራሮች እንዲስተካከሉ ለጥናት የሚሆኑ መነሻ ሀሳቦችን በማመንጨት የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፤ ይህንኑ ለኮምሽኑ እንዲያውቀው ያደርጋል፤ በራሱ ወይም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ጥናት በማድረግ አማራጭ ሀሳቦችን ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፭. ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን የአስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ እንዲሻሻል የመስሪያ ቤቱን ወይም የድርጅቱን የበላይ ኃላፊ ያማክራል፤ በመስሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ አገልግሎት አሰጣጥ መድሎ እንዳይፈፀም ይከታተላል፣ መድልዎ ተፈጽሞ ሲገኝ ለኮሚሽኑ እና ለተቋሙ ያሳዉቃል፡፡

2. follow-up the observance of anti-corruption policies, anti-corruption laws, rules and regulations of the public office or public enterprise; and advice the head of the public office or the public enterprise on their implementation;

3. prepares the code of conduct for the officers and employees of the public office or public enterprise together with the relevant departments, approves it in the institution and monitors its implementation following regulations of the code of conduct issued by the Commission;

4. initiate and submit research proposal to the Commission and make the head of the public office or the public enterprise know the same immediately conduct research on ways of correcting working methods vulnerable to corruption and impropriety on its own or with the collaboration of others and submit recommendations to the head of public office or the public enterprise and, upon approval follow-up its implementation;

5. incorporation with the relevant work units, advises the head of the public office or the public enterprise on ways of improving the administration and service delivery of the office or the enterprise with the view to making them responsive to the public; see to it that there is no partiality in service delivery; and report to the head of the office or enterprise, on any findings of such partiality.

፮. የሙስና ወንጀል ስለመፈፀሙ የሚያሳይ በቂ ማረጋገጫ ሲገኝ ወይም ራሱ ጥርጣሬ ሲኖረው ወይም ከሌሎች ወገኖች የሚቀርቡ ጥቆማዎች ካሉ ተቀብሎ ይመዘግባል፣ ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፣ ይህንኑ ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፣ ጉዳዩ የደረሰበትን ሁኔታ ይከታተላል፤

፯. በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ውስጥ ሥነ ምግባር እንዲዳብር የኃላፊነት ስሜት እንዲጎለብትና ሙስናን ለማጋለጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለማበረታታት ሠራተኞቻቸውን ከቂም በቀል እርምጃ ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት በሚዘረጋበት ሁኔታ ላይ የመሥሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የበላይ ኃላፊን ያማክራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፰. የሥነ ምግባር ጥሰቶችን የሚመለከቱ ጥቆማዎችን ተቀብሎ በማጣራት በቀጣይነት መደረግ ስለሚገባው ምርመራና መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም ለኮሚሽኑ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ስለአፈፃፀሙ ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፤

6. record and report to the Commission and make the head of public office or public enterprise know the same immediately, any incident of corruption it has observed or brought to its attention through whistle blowing, and follow up the status of the case;

7. advise the head of the public office or public enterprise on the way of promoting ethics, strengthening sense of duty and protection of employees from reprisal to encourage activities to expose corrupt measures so as to encourage disclosure of corruption, and follow-up the implementation of the same;

8. Receives and verify reports on ethical violations and submits proposed measure to the head of the institution or the Commission about the investigation that should be done and the action that should be taken; follow-up the implementation, and submits a report about the implementation to the head of the public office or public enterprise;

፱. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) የተጠቀሰው ጥፋት ከባድ የሥ-ነምግባር መጣስ ነው ብሎ ካመነ ወይም ከባድ የሥነ-ምግባር መጣስ መሆኑ የታወቀው ምርመራ ከተደረገ በኋላ ከሆነ እንደ ታወቀ ወዲያውኑ ጉዳዩን ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፤ ይህንኑ ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፤

፲. የሠራተኛ ቅጥር፣ እድገት፣ ዝውውር ፣ ስልጠና ሂደት ፣ የንብረት ወይም የአገልግሎት ግዥን ወይም የማንኛውም ሌላ ውል ይዘት አግባብነት ያለውን ሕግ ጥሷል ብሎ ሲያምን ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ ስለአፈፃፀሙ ለኮሚሽኑ ሪፖርት ያደርጋል፤

፲፩.ሠራተኛው የሙስና ወንጀልና ከመልካም ሥነ ምግባር ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶችን በማጋለጡ ማንኛውም ተጽዕኖ እንዳይደርስበት ክትትል ያደርጋል፤ ተጽዕኖ ያደረገ ወይም የቀጣ ወይም ተጽዕኖ ለማድረግ ወይም ለመቅጣት የሞከረ ካለ እያጣራ ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር ድርጊቱን ለኮሚሽኑ እና ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፤ ስለሚወሰድበት እርምጃ ይከታተላል፤ ተጽዕኖ አድራጊው የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሲሆን ጉዳዩን ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፤ በኮሚሽኑ የሚሰጠውን ውሳኔ ያስፈጽማል፤

9. Where it is believes that the ethical violation referred in sub article (8) of this article is a serious breach of ethics, or if it is found to be serious breach of ethics after an investigation, report same to the Commission immediately and make the head of the public office or the public enterprise know same;

10. When it believes that employee recruitment, promotion, transfer, training process, property or service purchase or any other content of contract violates the relevant law, it makes a recommendation to the head of the public office or the public enterprise for corrective action to be taken; it also monitors its implementation. reports to the Commission the performance thereof;

11. Make a follow up in order to make sure an employee who expose corruption crime and acts contrary to good morals will not be subject to any influence; shall investigate the case and with concrete evidence report the act to the Commission and to the head of the institution if there is any person who influenced or punished or tried to influence or punish the employee; it reports the matter to the commission when the person who is making an influence is the head of the institution; and it executes the decisions made by the Commission there to;

፲፪.በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ የሥነ ምግባር ጉዳዮች ወይም ችግሮች ላይ ሠራተኛው ወቅታዊ ውይይት እንዲያደርግ የመሥሪያ ቤቱን ወይም የልማት ድርጅቱን የበላይ ኃላፊ ያሳስባል፤

፲፫.በራሱ ወይም በውጭ ወይም በውስጥ ኦዲተሮች እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወይም እንዲስተካከሉ ሪፖርት በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ ስለተወሰደው እርምጃ እንዲሁም የዲሲፕሊንና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የሚያስተላልፏቸው ሪፖርቶችና ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ክትትል በማድረግ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ እንዲሁም በግልባጭ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ ተቆጣጣሪ አካልና ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፤

፲፬.በሕግ በሚወጣ መስፈርት መሰረት ሙስናን ወይም ብልሹ አሰራርን በመዋጋት ግንባር ቀደም የሆኑ አርአያነት ያላቸውን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ዝርዝር መረጃ መዝግቦ ይይዛል፤ ለኮሚሽኑ ይሰጣል፤

፲፭.ሥነ-ምግባርን በማስፈንና ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመዋጋት ረገድ በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ያቀናጃል፤ ያስተባብራል፤

12. Urges the head of the office or the development organization to have a timely discussion with the employee on the ethical issues or problems of the office or the development organization;

13. Monitors the action taken on matters that have been reported a measure to be taken or correction to be made by itself or external or internal auditors, as well as reports and decisions made by the disciplinary and grievance committees, and informs the head of the public office or the public enterprise and the copy to the supervisory body of the public office or the public enterprise and the Commission;

14. records the detailed information of the superior officers of the institution and employees who are leading role models in fighting corruption or malpractice in accordance with the requirements of the law; shall give the same to the Commission;

15. Coordinates activities which promote ethics and fighting corruption and malpractice in the public office or the public enterprise;

፲፮.በሃብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ሕግና አሰራር የየተቋሙ አመራሮችንና ሠራተኞች መረጃዎችን ያደራጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ ሀብታቸውን እንዲያሳውቁ፣ እንዲያስመዘግቡ፣ እንዲያሳድሱ ያደርጋል፤ የምዝገባ ሰነዱንም ለኮሚሽኑ ይልካል፤ ከኮሚሽኑ ፀድቆ የተላከውን የሃብት ምዝገባ ሰርተፊኬት ለአስመዝጋቢው ይሰጣል፤

፲፯.በተቋሙ አዲስ የተሾሙ፣ የተቀጠሩ አመራሮችና ሠራተኞች ሥራ ከመጀመራቸው ወይም የቅጥር ፎርም ከመሙላታቸው በፊት ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ያደርጋል፣

፲፰.በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሀብት አስመዝጋቢዎች አገልግሎት ሲያቋርጡ ከሥራ ክፍሉ ክሊራንስ እንዲወስዱ ያደርጋል፤ በተቋሙ አገልግሎት ለሚያቋርጡ የሀብት አስመዝጋቢዎች በህጉ መሰረት ዳግም ምዝገባ እንዲያከናውኑ በማድረግ ሰርተፊኬትና ክሊራንስ ይሰጣል፣ ይህንኑ ለኮሚሽኑ ያሳውቃል፤

፲፱.በመልካም ሥነ-ምግባርና ሙስና መከላከል ዙሪያ ግንዛቤ የሚፈጥሩ መልዕክቶች የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲተላለፉ ያደርጋል፤

፳. በየበጀት ዓመቱ ስለሚያከናውናቸው ተግባሮች ዕቅድ፣ መርሀ ግብርና በጀት አዘጋጅቶ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊና ለኮሚሽኑ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

16. In accordance with the laws and procedures of asset reporting and registration, organizes the information, updates it, informs, registers and updates assets of the management staff and employees of each institution ; shall also send the registration document to the Commission; and give the asset registration certificate approved by the commission to the registrant;

17. Shall make newly appointed and hired managers and employees of the institution to register their assets before starting work or fill employment forms.

18. shall cause asset registrants in the institution to obtain clearance from the office upon termination of their service; It issues certificates and clearances to wealth registrants who terminate their services in accordance with the law, and informs the Commission;

19. disseminate messages which create awareness about good ethics and prevention of corruption using different methods;

20. Prepares a plan, program and budget for the activities to be carried out every fiscal year and submits it to the head of the public office or the public enterprise and the commission, and implements it when approved;

፳፩.በክፍሉ ስለተከናወኑ ተግባራት፣ ስላጋጠሙ ችግሮችና ስለተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች በወቅቱ ሪፖርት በማዘጋጀት ለኮሚሽኑ እና ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፤

፳፪.አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተለይተው የሚሰጡትን ሥነ-ምግባርን የሚመለከቱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## ፲. የሥነ-ምግባር መኮንን ኃላፊነት

የመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት የሥነ-ምግባር መኮንን በዚህ ደንብ ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የተሰጡትን ተግባራት ያስፈጽማል፡፡

## ፲፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ኃላፊ ኃላፊነት

የየተቋማቱ የበላይ ኃላፊ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. በተቋሙ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው የሥራ መሪ፣ ሠራተኛ እና የሰመረ የሥራ ግንኙነት እንዲኖርና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ክትትል የማድረግ፤

፪. የአሰራር ሥርዓት ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የማይመች ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን የማድረግ፤

፫. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው አኳኋን ምቹ የሥራ ሁኔታን የመፍጠር፤

፬. የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ፣ የሙስናና የብልሹ አሰራር ዝንባሌዎች ሲታዩ በፍጥነት ከሰራተኞቹና ከሥራ መሪዎች ጋር የመመካከርና መፍትሔ የመሻት፤

21. prepare a timely report on the activities carried out by the unit, the problems encountered and the remedial measures taken and submit it to the commission and the head of the institution;
22. Performs other duties related to ethics as specified by the relevant law.

## 10. Responsibilities of the Ethics Officer

The ethics officer of a public office or the public enterprise shall carry out the duties assigned to the ethics liaison unit in this regulation.

## 11. Responsibilities of the head of the government office or public enterprise

The head of each institution shall have the following responsibilities:

1. Follow up that officer and employee of the institution pursue good ethical conduct, good working leader and employee relationship are established and good governance is maintained;
2. Ensure that the functioning of the institution is based on transparency so that it may not vulnerable to corruption and impropriety;
3. create a conducive work condition which enables the ethics liaison unit to carry out its responsibilities;
4. discuss with the officer and employee of the institution and seek solutions when trends of indiscipline, corruption and impropriety appear in the institution ;

፭. የሚወሰዱ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችና የዲሲፕሊን እርምጃዎች በበቂ ማስረጃ የተደገፈ፣ ከቂም በቀል የፀዳ፣ በተቋማቱ መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆናቸውን፣ እርምጃዎቹ ሕግንና መመሪያን መሰረት ያደረጉና ፍትሐዊ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

፮. የመከታተያ ክፍሉ ለሠራተኛው በቂ የሥነ-ምግባር ትምህርት በየጊዜው መስጠቱን፣ ብልሹ አሰራሮችን ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን በበቂ ሁኔታ ተከታትሎ በማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረጉን የመከታተል፣ የመቆጣጠር፤

፯. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉን የእለት ከዕለት ተግባር ይመራል፤ በሥራ ክፍሉ የሚመጡ ሪፖርቶችን ተቀብሎ ይመለከታል፤ መፈጸም ባለባቸው ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ይሰጣል፤

፰.የጠቋሚዎችን የጥበቃ ሥርዓት የመዘርጋትና የጠቋሚዎችን መብቶችና ግዴታዎች በተለይም የሚከተሉትን የሚመለከት ማስታወቂያ በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ በጉልህ እንዲለጠፍ የማድረግ፤

ሀ) ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የማጋለጥ ግዴታ ያለበት መሆኑንና አለማጋለጥ የሚያስጠይቅ መሆኑን፣

5. ensure that the administrative decision and disciplinary measures taken are supported by sufficient evidence, free from malice, and contribute to the good governance of the institutions, and that the measures are based on laws and guidelines and are fair;

6. follow up and ensure that the Ethics Liaison Unit is providing the employee with adequate ethics education, watching out corrupt practices and impropriety and following up the taking of corrective measures;

7. Leads the day-to-day operations of the Ethics liaison unit; Receives and reviews reports from the work department. Provides direction on matters to be carried out;

8. Ensure that the system for the protection of whistle blowers is established and notice explaining, in particular, the following rights and duties of whistle blowers are clearly posted at conspicuous place:

   a. that every official or employee shall expose corruption and failure to do so entails liability;

ለ) ጥቆማዎች በአካል ቀርበው በቃል ወይም በጽሁፍ ፣ ስምን ገልፆ ወይም ሳይገለጽ በስልክ ፣ በፖስታ፣ በኢ-ሜል፣ በፋክስ ወይም በመሳሰሉት ኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎች ሊቀርቡ የሚችሉ መሆኑን፣

ሐ) በሥነ-ምግባር ደንብ ጥሰት ወይም በሙስና ወንጀል ጠቋሚዎች ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለና ተፈጽሞ ከተገኘ በአስተዳደርና በወንጀል የሚያስጠየቅ መሆኑን፣

መ) ሆን ብሎ ሰውን ለማጥቃት በሀሰት የተዘጋጀ ወይም የተቀነባበረ ጥቆማ በአስተዳደርና በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን፣

ሠ) የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ የቂም በቀል እርምጃዎችን የሚመረምርና የሚያቀርብ መሆኑን፤

፱. ለክትትል እንዲያመች በውጭና በውስጥ ኦዲተሮች እርምጃ እንዲወሰድባቸው ወይም እንዲስተካከሉ ሪፖርት የቀረበባቸው ጉዳዮችን የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሉ በግልባጭ እንዲያውቃቸው ማድረግ፤

፲. እንደየ አግባብነቱ የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ኃላፊ ወይም ቡድን ወይም ባለሙያ በማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሳባ ያለድምፅ እንዲሳተፍ ያደርጋል፤ ሆኖም በእቃ ግዥ፣ በሎጀስቲክስ አቅርቦት፣ በሰው ሀይል ቅጥር እና በመሳሰሉት ሥራዎች በኮሚቴ አባልነት እንዳይሳተፉ ያደርጋል፤

b. that disclosure of corruption may be made orally by appearing in person or by telephone, mail, e-mail, fax and such other ar electronic media with or without disclosing ;

c. that taking retaliatory action against whistleblowers of ethical violations or corruption is prohibited and will be prosecuted administratively and criminally if found to have been committed;

d. That unfounded disclosure intended or designed to harm another person entails administrative and criminal liability.

e. that the ethics liaison unit shall conduct investigates and reports retaliation;

9. to facilitate monitoring make the ethics liaison unit be aware of the issues that have been reported for action or correction by the external and internal auditors;

10. As it deems necessary, let the head of the ethics liaison unit or a team or expert to participate in the meeting of the management committee without a vote; However, do not let them participate as a committee member in the procurement of goods, supply of logistics, employment of human resources and the like;

፲፩.የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ለሥራው ጠቃሚ የሆነ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኝ ተገቢውን ድገፍ የማድረግ፣

፲፪.የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ የሚፈለገውን ትብብር በተሟላ ሁኔታ እንዲያገኝ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፡፡

**፲፪.<u>የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ሠራተኞች ኃላፊነት</u>**

፩. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ሠራተኛ የመሥሪያ ቤቱ ወይም የድርጅቱ የሥነ-ምግባር የሥራ ክፍል ለሥራው የሚፈልጋቸውንና የሚጠይቃቸውን መረጃዎችና ድጋፎች በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፤

፪. ትብብር ስለመከልከል በሌሎች ሕጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ለሥነ ምግባር መኮንኑ ትብብር መከልከል አስተዳደራዊ ተጠያቂነትን ያስከትላል።

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የቅጥርና የሥራ ሁኔታ</u>**

**፲፫. <u>የኃላፊና ሠራተኞች አመዳደብ</u>**

፩. በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በተቋማት ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የመመደብ፣ የመቅጠር፣ የማዛወር እና የማሰናበት ተግባር የኮሚሽኑ ይሆናል፤

11. To provide appropriate support for the ethics liaison unit to receive education and training that is useful for its work.
12. Facilitating the conditions for the ethics liaison unit to obtain the required cooperation in full.

**12. <u>Responsibility of public office or public enterprise employees</u>**

1. Any employee of a public office or public enterprise is obliged to cooperate by providing the information and support that the ethics liaison unit of the office or enterprise needs and requests for their work;
2. Subject to the provisions of other laws on non-cooperation, Refusing to cooperate with the ethics officer will result in administrative liability.

**<u>Part three</u>**

**<u>Ethical Liaison Unit of employment and working conditions</u>**

**13. <u>Placement of officials and workers</u>**

1. According to sub article (3) of article 19 of the proclamation , the task of assigning, hiring, transferring and dismissing the head of the ethics liaison unit or employee in institutions shall be the responsibility of the commission;

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ኮሚሽኑ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የመመደብ፣ የመቅጠር፣ የማዛወር እና የማሰናበት ተግባር ሲያከናውን በቅድሚያ የአስተዳደሩ የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ ወይም የአስተዳደሩ የልማት ድርጅት ወይም የተቋማቱ ማኔጅመንት እንዲመክርበት ይደረጋል፤

፫. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሥራ ደረጃ በአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ወይም በአስተዳደሩ የልማት ድርጅቱ በሚገኙ ዓላማ ፈጻሚ የሥራ ደረጃ ጋር ትይዩ ይሆናል፤

፬. የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ለሥራ መደቡ የሚያስፈልገው የትምህርትና የሥራ ልምድ እንዲሁም የሥነ-ምግባር ሁኔታ ለልማት ድርጅት ሲሆን በድርጅቱ ደንብና መመሪያ፣ ለመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሆን በከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኛ ሕግ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ መሠረት ይወሰናል፤

፭. የቅጥር፣ የዕድገት ወይም የዝውውር ዝርዝር አፈጻጸም እንደሁኔታው በከተማው አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች ህግ ወይም በመንግስት መስሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ሠራተኛ አስተዳደር ደንብ ወይም በህብረት ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

2. Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this article, when the Commission carries out the task of assigning, hiring, transferring and dismissing the head or employee of the ethics liaison unit, the government office of the administration, or the public enterprise of the administration or the management of the institutions shall be consulted first;

3. The work level of ethics Liaison Units shall be parallel to the work level to objective executor of the Public office or public enterprise;

4. Without prejudice to the provisions of Article 14 of this regulation, the educational and work experience and ethical conditions required for the position are determined by the rules and guidelines of public enterprise or by the city administration's civil servant law other appropriate law in case of a public office;

5. The implementation of employment, promotion or transfer list shall be according to the City Government Civil Service Law or the public office or the public enterprise's labor management regulation or union agreement as the case may be.

**፲፬. በሥነ-ምግባር የመከታተያ ክፍል ለመመደብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች**

፩. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሆኖ የሚመደብ ሰው፣

ሀ) በሥነ-ምግባሩ በአካባቢው የተመሰገነ፣

ለ) ሙስናና ብልሹ አሠራርን የሚጸየፍና በዚህ አቋሙ የታወቀ፣ እና

ሐ) ከአደንዛዥ ዕጽና መጠጥ ሱሰኝነት የራቀ እና በዚህ ጽኑ አቋሙ በህብረተሰቡ የታወቀ፣ መሆን አለበት፤

፪. በማንኛውም ተቋም ውስጥ በሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሆኖ የሚመደብ ሰው በተቻለ መጠን በሥነ-ምግባር፣ በሕግ፣ በፍልስፍና፣ በፖለቲካል ሳይንስ፣ በሥነ-ማህበረሰብ፣ በሥራ አመራር፣ በሂሳብ አያያዝ ወይም ከተቋሙ ሥራዎች ጋር ተያያዥነት ባለው ሌላ ተዛማጅ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በላይ የተመረቀ መሆን ይኖርበታል፡፡

**፲፭. ስለ ደረጃ እድገትና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች**

፩. በተቋማት ውስጥ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሆኖ የተቀጠረ ወይም የተመደበ ማንኛውም ሰው በመስሪያ ቤት ወይም በድርጅቱ ደንብና መመርያ መሰረት ለደረጃ እድገት የመወዳደር መብቱ የተጠበቀ ነው፤

፪. ለሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ሠራተኞች ተፈጻሚ የሚሆኑ ጥቅማ ጥቅሞች ለሥነ-ምግባር መከታተያ ሠራተኞች ተፈጻሚ ይሆናል፤

**14. Requirement for placement of Ethics Liaison Unit**

1. A person to be placed as the head or employee of the ethics department shall:
   a) be commendable for his high ethical standard,
   b) have manifest hatred for corruption and impropriety and be reputed by society as such,
   c) be free from drug and alcohol addiction be reputed by society as such;
2. A person to be placed as the head or employee of the ethics liaison unit in any institution shall have as far as possible bachelor’s degree or above in ethics, law, philosophy, political science, sociology, management, accounting or any other field related the function of the institution's..

**15. promotion and other benefits**

1. Any person who is employed or placed as the head or employee of the ethics department in institutions shall be entitled to promotion according with the relevant rules and regulations of the public office or public enterprise;
2. Benefits applicable to other employees of the public office or the public enterprise shall be applicable to the employees of the ethics department;

፫. ልዩ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ወይም በሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊነት ወይም የስነ-ምግባር መኮንንነት የሥራ ልምድ በማንኛውም መሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የስራ ክፍል ውስጥ እንደተሰራ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## ፲፮. ስለመደበኛ ሥራ

የሥነ-ምግባር መከታተያ ኃላፊ ወይም የሥነ-ምግባር ሠራተኛው ሥራውን የሚያከናውነው በሙሉ የሥራ ጊዜው ይሆናል::

## ፲፯. የፕሮሰስ ካንውስል አባል ስለመሆን

የሥነ- ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ቡድን መሪ ወይም ባለሙያ የሥነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከልን በተመለከተ በመስሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ወይም በቅርንጫፉ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖረው እና ተፈፃሚነታቸውን ለመከታተል በተቋሙ ወይም በቅርንጫፉ የፕሮሰስ ካውንስል ላይ ያለድምፅ ይሳተፋል፡፡

## ክፍል አራት

## የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ

## ፲፰. የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ

፩. የሥነ-ሥርዓት እና የዲስፕሊን ጉድለት እርምጃ አወሳሰድ የሚጀመረው በሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ላይ በሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ተገልጋዮች በሚያቀርቡት አቤቱታ ወይም ተግባሩን ሲያከናውን በፈፃማቸው ግድፈቶች ወይም በተደረገ ክትትል ላይ ተመስርቶ ይሆናል፤

3. Unless there is a special situation or as stipulated by another law, the work experience of ethics liaison unit or ethics officer is considered as relevant work experience done in any department of public office or the public enterprise.

## 16. Regular work

The Head of the Ethics Unit or the Ethics unit employee shall carry out his duties on a full time basis.

## 17. Being a member of the Council of Process

The head of the ethics liaison unit or the leader of the team or an expert participates in the process council of the institution or the branch, without vote, to have a complete understanding of the decisions made by the public office or public enterprise or the branch regarding the construction of ethics and anti-corruption and to monitor their implementation.

## Part four

## Disciplinary Measures

## 18. Taking of disciplinary measures

1. Procedures and disciplinary measure may be initiated based on suggestions or complaints made by customers or on the basis of monitoring or omissions in the performance of the duties;

፪. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በሥ-ነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ላይ የዲሲፒሊን ግድፈት ተፈፅሟል የሚል ጥቆማ ሲደርሰው ለኮሚሽኑ ይልካል፤

፫. ኮሚሽኑ በመከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ላይ የዲሲፕሊን ግድፈት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሰረት ሲደረሰው ተቀብሎ ያጣራል፤

፬. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የዲሲፕሊን ግድፈት የፈጸመ መሆኑ በኮሚሽኑ ሲረጋገጥ አግባብ ባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ሕግ መሰረት በዲሲፕሊን እንዲጠየቅ ያደርጋል፤

፭. ኮሚሽኑ የዲሲፕሊን ክስ የሚቀርብበትን ቦታ ይወስናል፤

፮. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ የዲሲፕሊን ክስ ሂደት በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ሠራተኞች የዲሲፕሊን ክስ በሚመራበት አግባብ መመራቱን ኮሚሽኑ ክትትል ያደርጋል፤

፯. ኮሚሽኑ የሥነ ምግባር መከታተያ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የፈጸመው ተግባር በወንጀል የሚያስቀጣው ሆኖ ካገኘው በወንጀል እንዲጠየቅ ያደርጋል፡፡

2. When the head of the institution receives a suggestion that a disciplinary violation has been committed by the head of the ethics liaison unit or an employee, he shall send the suggestion to the Commission;
3. in accordance with sub-article (1) and (2) of this article the Commission will receive and investigate disciplinary breach by the head or employee of the ethics liaison unit;
4. When it is confirmed by the commission that the head of the ethics liaison unit or an employee has committed disciplinary breach, he will be subject to disciplinary action according to the relevant public office or public enterprise law;
5. The Commission shall determine the venue of the disciplinary proceedings;
6. The Commission will monitor whether the disciplinary proceedings of the ethics liaison unit head or employee are conducted in the same manner as the disciplinary proceedings of the employees of the public office or public enterprise;
7. If the Commission finds that the conduct of the head of the ethics department or an employee is punishable by a crime, it shall make them liable accordingly.

## ፲፱. ከስራ ስለማሰናበት

፩. የሥነ-ምግባር መከታተያ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ከባድ የሥነ-ምግባር ጥሰት የፈጸመ መሆኑ ተረጋግጦ ከሥራው እንዲሰናበት አግባብነት ባለው ሕግና በመሥሪያ ቤቱ ወይም በልማት ድርጅቱ ደንብ መሠረት ሲወሰን ከሥራው ይሰናበታል፤ ኮሚሽኑ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፪. የሥነ ምግባር መከታተያ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የፈጸመው የዲሲፕሊን ጥፋት ከሥራ እንዲሰናበት የሚያደርገው ባይሆንም ከሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል እንዲነሳ ኮሚሽኑ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ከሥነ ምግባር መከታተያ ኃላፊነት ወይም ሠራተኝነቱ እንዲነሳ የተደረገው ሠራተኛ በሚያሟላው ሌላ የስራ መደብ ላይ እንዲመደብ ኮሚሽኑ አግባብነት ላለው ተቋም ይልካል፤

፬. የመሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ በሥነ-ምግባር መከታተያ ኃላፊው ወይም ሠራተኛው ላይ የተላፈውን ከሥራ የማሰናበት ውሳኔ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለልማት ድርጅቱ ሠራተኞች በተገኘው ማናቸውም ዘዴ ያሳውቃል፡፡ ኮሚሽኑ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

## 19. Dismissal

1. When it is confirmed that the head of the ethics liaison unit or an employee has committed a serious violation of ethics and it is decided to dismiss him from his job according to the relevant law and the regulations of the public office or public enterprise, he will be dismissed from his job; the Commission will monitor its execution;
2. Even if the disciplinary offense committed by the head of the ethics liaison unit or an employee does not lead to his dismissal, the Commission may issue a decision to remove him from the ethics liaison unit;
3. Pursuant to sub- article (2) of this article, the Commission will send the employee who is removed from the responsibility of the ethics liaison unit to the appropriate institution to be assigned for another job position;
4. The head of the public office or public enterprise informs the employees of the public office or public enterprise the dismissal decision passed on the head of the ethics liaison unit or the employee by any means available. The Commission will monitor its performance.

**፳. ስለቅሬታ አቀራረብና ስለይግባኝ**

፩. የሥነ-ምግባር የስራ መከታተያ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ከሥራው የታገደበት ወይም የተነሳበት ምክንያት አለአግባብ ነው ብሎ ካመነ አግባብ ባለው ሕግና በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም የልማት ድርጅቱ ደንብ ወይም የህብረት ስምምነት መሠረት ሥነ-ሥርዓቱን ተከትሎ ቅሬታ ወይም ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፤

፪. በቀረበው ቅሬታ ወይም ይግባኝ መሠረት የተወሰደው እርምጃ ተገቢ አለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ይህንኑ ለሠራተኛው በተገኘው ማናቸውም ዘዴ ማሳወቅ አለበት፡፡

**ክፍል አምስት**

**የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችና የኮሚሽኑ የስራ ግንኙነት**

**፳፩. ትብብር**

በዚህ ደንብ በሌሎች አንቀጾች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚሽኑ፡-

፩. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋማት የሥነ-ምግባር ትምህርትን ለማስፋፋትና ሙስናን ለመከላከል በሚያደርጉት ጥረት የቴክኒክና የሙያ ዕገዛ ያደርጋል፣ ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፪. ከተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎችና የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ጋራ የሚወያይበት የጋራ መድረክ በማዘጋጀት በተከናወኑ ተግባራትና ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ይወያያል፤

**20. Grievance and Appeals**

1. If the head of the ethics liaison unit or an employee believes that the reason for his suspension or removal from his job is inappropriate, he may file a complaint or appeal following the procedure in accordance with the relevant law and the regulations of the public office or public enterprise or the union agreement;
2. If the action taken based on the complaint or appeal is confirmed to be inappropriate, the head of the institution must inform the employee by any means available.

**Part five**

**Relationship of Ethics Liaison Unit and the Commission**

**21. Cooperation**

Without prejudice to other provisions of these this regulations, the Commission shall:

1. provide technical and professional assistance to ethics liaison unit in their efforts to promote ethics education and prevent corruption in institutions and prepare and offer training program to them ;
2. organize joint forums where heads of institution and ethics liaison unit deliberate on activities carried out and problems encountered;

፫. በስነ-ምግባር መከታታያ ክፍሎች በሚቀርቡ ሌሎች የትብብርና የድጋፍ ጥያቄዎች መሰረት አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**፳፪. <u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>**

፩. የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ፡-

ሀ) በተቋማቱ የሥነ-ምግባር ትምህርቶችን በመስጠት ረገድ ስለተሰሩ ሥራዎችና ስላጋጠሙ ችግሮች፣

ለ) በተቋማቱ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮችን ለማስተካከል ስለተወሰዱ እርምጃዎችና ስላጋጠሙ ችግሮች፣

ሐ) በተቋማቱ ስለተከሰቱ የሙስና ወይም የብልሹ አሠራር ችግሮች፣ ስለተወሰዱ እርምጃዎች ወይም ሁኔታው ስላለበት ደረጃ፣

መ) ከሌሎች አካላት ስለተደረጉ ድጋፎችና ትብብሮች፣ እና

ሠ) የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱን፤ በወቅቱ ለተቋሙ እና ለኮሚሽኑ ያቀርባል፤

፪.የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ በሪፖርት ላይ ከኮሚሽኑ እና ከተቋሙ የሚሰጠውን ግብረ መልስ ይተገብራል፡፡

**<u>ክፍል ስድስት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**፳፫. <u>የቂም በቀል እርምጃ ስለመከልከሉ</u>**

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል የተሰጡትን ተግባራት በማከናወኑ ምክንያት በሥነ-ምግባር መኮንን ላይ የቂም በቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው፤

3. cooperate and provide such other necessary assistance to the ethics liaison unit upon request.

**22. <u>Reporting</u>**

1. any ethics liaison unit shall submit quarterly and annual reports to the institution and the commission in due course:
   a) an activates carried out and the problems encountered with respect education relating to corruption;
   b) on measures taken to correct working procedures of the institution exposed to risks of corruption and impropriety and problem encounter;
   c) on measures taken following the corruption or impropriety problems in the institution or the state of the case;
   d) Support and cooperation from other parties, and
   e) shall submit the report to the institution and the Commission in due course;
2. The ethics liaison unit shall apply the feedback from the Commission and the Institution on the report.

**<u>Part six</u>**

**<u>Miscellaneous provisions</u>**

**23. <u>prohibition of reprisal measure</u>**

1. Taking any reprisal measures against an ethics officer due to his performance of functions entrusted to Ethics Liaison Unit under Article 9 of this regulation is prohibited;

፪. የቂም በቀል እርምጃ የተወሰደበት የሥነ-ምግባር መከታተያ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ የበቀል እርምጃው እንዲታገድለት ለኮሚሽኑ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤

፫. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ የቂም በቀል እርምጃ መወሰዱን ካረጋገጠ የበቀል እርምጃው እንዲቆም ትእዛዝ ይሰጣል፤

፬. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፪) ላይ የቂም በቀል እርምጃ የወሰደ አመራር ወይም ሠራተኛ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳፬. <u>ቅነሳ</u>**

ሠራተኛን መቀነስ ግዴታ በሚሆንበት ወቅት የልማት ድርጅት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በአሰሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ለሠራተኞች ተጠሪ የተሰጠው ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

**፳፭. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ ተግባራዊነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፮. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ይህንን ደንብ የሚቃረኑ የአስተዳደሩ ደንቦችና የአሠራር ልማዶች በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ፡፡

2. an ethics officer against whom a reprisal measure has been taken may apply to the Commission for the suspension of reprisal measure;
3. the Commission shall suspend any reprisal measure upon ascertain is existence by examining an application submitted to it in accordance with sub-article (2) of this Article ;
4. Any official or employee who took reprisal measure under sub-section (2) of this article shall be liable according to the relevant law.

**24. <u>Reduction</u>**

in situation where reduction of workers becomes imminent, the head and workers the Ethics Liaison Unit shall have the right according to worker’s representative in labor law.

**25. <u>Duty to cooperate</u>**

Any individual shall be duty-bound for the implementation of this Regulation.

**26. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any Regulation, directives, or customary practices of the City Administration which are inconsistent with his Regulation, shall have no effect.

**፳፯. <u>መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን</u>**

ኮሚሽኑ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፰. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከ መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**አዳነች አበቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**27.<u>Power to issue directives</u>**

The Commission may issue directive necessary for the implementation of this Regulation.

**28. <u>Effective date</u>**

This Regulation shall enter in to force as of this 16 th day of March 2023.

**Done at Addis Ababa, this 16 th day of March 2023**

**Adanech Abebe**

**Mayor of Addis Ababa city**